በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC
OF ETHIOPIA
FEDERAL HIGH COURT

ቁጥር No. ……………
……………ቀን ……… ዓ. ም.
Date 200 ——
አዲስ አበባ/Addis Ababa

የመ/ቁ. 03122
4/12/97

ዳኞች - ሙስጠፋ አህመድ
ሰለሞን አረዳ
ሐፊዝ አባጀማል

ከሣሽ ............ ልዩ ዐቃቤ ሕግ

ተከሣሾች ...... በእነ አበራ የማነአብ 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች ከማረሚያ ቤት ቀርበዋል :: ጠበቆቻቸውም ቀርበዋል ::

መዝገቡን መርምረን በ1ኛ ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች ላይ የሚከተለውን የቅጣት ውሣኔ ሰጥተናል :: በ1ኛ እና 3ኛ ተከሣሽ የተጣለው ቅጣት በዚህ መዝገብ እና በሠ/ቁ. 03/22/912/89 የተሰጡት የጥፋተኝነት ውሣኔዎች አንድ ላይ በማጣመር ነው

## የቅጣት ውሣኔ ፣

- 1ኛ ተከሣሽ ክ/ል ደበላ ዲንሳ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው በልዩ ዐቃቤ ሕግ የክስ ድርጊቶች በድርጊት 1-6 ፣ 8-16፣ 18 እና 21 የተመለከቱት በድምሩ 210 /ሁለት መቶ አስር/ ሰዎች በቀይሽብር በሚገደሉበት ወቅት የድርጊቱ ተካፋይ ስለመሆኑ በማስረጃ በመረጋገጡ እና የወ/መ/ሕ/ቁ. 32/1/ለ እና 281 ላይ የተመለከተውን ተላልፈው በመገኘ ታቸው ነው ::

እንዲሁም 1ኛ ተከሣሽ በወ/መ/ቁ. 03122 ጥፋተኛ ሆነው የተገኙት በልዩ ዐቃቤ ሕግ የክስ ድርጊቶች በድርጊት 2፣ 5፣ 7፣ 8፣ 9፣ 26 እና 27 የተመለከቱት 96 /ዘጠና ስድስት/ ሰዎች ያለፍርድ በሚገደሉበት ወቅት የድርጊቱ ተካፋይ ስለመሆናቸው በመረጋገጡ በወ/መ/ሕ/ቁ. 32/1/ለ እና 281 ለይ የተመለከተውን ተላልፈው በመገኘ ታቸው ነው ::

ለትክክል ግልባጭ



ስልክ Tel. 75 19 11 ፋክስ Fax: 75 53 99 ፖ. ሣ. ቁ. P. O. Box 3483

44

- 2ኛ ተከሣሽ አቶ አበራ የማነ አብ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው በልዩ ዐቃቤ ሕግ የክስ ድርጊቶች በድርጊት 1-6 እና 8-14 የተመለከቱት 145 /አንድ መቶ አርባ አምስት/ ሰዎች በሚገደሉበት ወቅት የድርጊቱ ተካፋይ ስለመሆናቸው በማስረጃ በመረጋገጡ የወ/መ/ሕ/ቁ. 32/1/ሀለ እና 281 ላይ የተመለከተውን ተላልፈው በመገኘታቸው ነው ፡፡

- 3ኛ ተከሣሽ ሻ/ቃ ሮንዳሳ ቢራቱ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኙት በልዩ ዐቃቤ ሕግ የክስ ድርጊቶች በድርጊት 1-6 እና 8-14 የተመለከቱት 145 /አንድ መቶ አርባ አምስት/ ሰዎች ያለፍርድ በሚገደሉበት ወቅት የድርጊቱ ተካፋይ ስለመሆኑ በማስረጃ በመረጋገጡ የወ//ሕ/ቁ. 32/1/ሀለ እና 281 ስር የተመለከተውን ተላልፈው በመገኘታቸው ነው ፡፡

እንዲሁም 3ኛ ተከሣሽ በወ/መ/ቁ. 03122 በድርጊት 2፣ 5፣ 7፣ 8፣ 9፣ 26 እና 27 የተመለከቱት 96/ዘጠና ስድስት / ሰዎች ያለፍርድ በሚገደሉበት ጊዜ የድርጊቱ ተካፋይ ስለመሆኑ በማስረጃ በመረጋገጡ የወ/መ/ሕ/ቁ. 32/1/ሀለ እና 281 ስር የተመለከተውን ተላልፈው በመገኘታቸቸው ነው ፡፡

የልዩ ዐቃቤ ሕግ በሰጠው የቅጣት አስተያየት ተከሣሾች የወንጀል ድርጊቱን የፈጸሙት በወቅቱ የተሰጣቸውን የመንግሥት ሥልጣን መከታ በማድረግ መሆኑ፡ ተከሣሾች በሰራቸው ያቋቋሟቸው ከፍተኞችና ቀበሌዎች ከሕግ ውጭ የሚፈጽሙት የዘር ማጥፋት የግድያ ወንጀል እንደ ሕጋዊ ተግባር እንዲመለከቱት የተለያዩ መመሪያዎችን በማስተላለፍ እንዲሁም ለሚፈጸሙት ተግባር የማሰቃያና የመግደያ መሣሪያዎችን በማቅረብ ሰዎች እንዲገደሉ በማድረጋቸው የሟቾች ሬሳ ደግሞ ረጅም ሰዓት በዝናብና በፀሐይ በመጣል ሽብር በሚያስከትል ሁኔታ የወንጀል ድርጊቱን የፈጸሙ በመሆኑ ፍ/ቤቱ እነዚህን ሁኔታዎች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በተከሣሾች ላይ የሚጣለውን ቅጣት አክብዶ እንዲወሰንልን በማለት አመልክተዋል ፡፡

1ኛው ተከሣሽ በሰጠው የቅጣት አስተያየት የቀረበብኝ የወንጀል ሪከርድ አለመኖሩ፣ የብዙ ቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኔ፣ እረጅም ዘመናት ሀገሬን ያገለገልኩ መሆኔ፡ በማረሚያ ቤት ቆይታዬ ብዙ ግልጋሎቶች የሰጠሁ መሆኔን እና ያሳየሁትን ለመታረም ያለኝን ዝግጅነት እና በብዙ በሽታ እየተሰቃየሁ ያለ መሆኑ ፍ/ቤቱ እነዚህን ሁኔታዉች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በእኔ ላይ የሚጣለውን ቅጣት አቅሎ እንዲወስንልኝ በማለት አመልክተዋል ፡፡

2ኛ ተከሣሽ በሰጡት የቅጣት አስተያየት የቀረበብኝ የወንጀል ሪከርድ አለመሀ ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኔ፣ ከተማሪነት ጊዜዬ ጀምሮ ለሀገሬ ብዙ አስተዋጽኦ ያደረኩ መሆኔ፣ በማረሚያ ቤት ቆይታዬም የተለያዩ ማህበራዊ ግልጋሎቶችን ያበረከትኩ መሆኑ በቀይ ሽብር ዘመን ለተፈጸመውም እጅግ የማዝንና የተጸጸትኩ መሆኑን ፍ/ቤቱ እነዚህን ሁኔታዎች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በእኔ ላይ የሚጣለውን ቅጣት አቅሎ እንዲወስንልኝ በማለት አመልክተዋል ፡፡

ለትክክል ግልባጭ



45

3ኛው ተከሣሽ በሰጡት የቅጣት አስተያየት የቀረበብኝ የወንጀል ሪከርድ አለመኖሩ፣ በእድሜዬ የገፋሁ የ70 ዓመት አዛውንት መሆኔ፣ ሀገሬን ለብዙ ዘመናት ያገለገልኩ መሆኔ ፣ በብዙ በሽታ እየተሰቃየሁ የምገኝ መሆኔ፣ በማረሚያ ቤት ቆይታዬ ብዙ የተማርኩ እና የተለያዩ ማህበራዊ ግልጋሎቶችን ያበረከትኩ መሆኔ ፍ/ቤቱ እነዚህን ሁኔታዎች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በእኔ ላይ የሚጣለውን ቅጣት አቅሎ እንዲወስንልኝ በማለት አመልክተዋል ::

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙ ያቀረቡትን የቅጣት አስተያየት እንደሚከተለው መርምሮታል::

ተከሣሾች የወንጀል ድርጊቱን የፈጸሙት በወቅቱ የነበራቸውን የመንግሥት ኃላፊነት መከታ በማድረግ መሆኑ ተጎጂዎች ደግሞ በቁጥር ስር የነበሩ ሰዎች መሆናቸው እነዚህ ሁኔታዎች በተከሰሱበት ላይ የሚጣለውን ቅጣት የሚያከብዱ ሁኔታዎች ሆነው አግኝተናል ::

በሌላ በኩል በተከሳሾች ላይ የቀረበ የወንጀል ሪኮርድ አለመኖሩ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸው፣ ማረሚያ ቤት በቆዩባቸው ጊዜያት ለመታረም ያሳዩት ዝግጁነት እነዚህ ሁኔታዎች በተከሳሾች ላይ የሚጣለውን ቅጣት የሚያቀሉ ምክንያቶች ሆነው አግኝተናል::

ቅጣት ሊወሰን የሚገባው ያጥፊውን ያደገኛነት ጠባይ እንደመጠኑ በመገመት፣ ያለፈ የህይወት ታሪኩን፣ ለማጥፋት ያነሳሱትን ምክንያቶችና ያሳቡን አላማ፣ የግል ኑሮውን ሁኔታና የትምህርቱን ደረጃ እንዲሁም የጥፋቱን ከባድነትና ያፈፃፀሙን ሁኔታዎች በመገመት በራሱ አጥፊነት መሠረት መሆኑን በህጉ ላይ ተመልክቷል:: በመሆኑም ተከሣሾች ጥፋተኛ የተባለት የወንጀል ድርጊት ሲፈፅሙ ያፈፃፀማቸው ሁኔታና የተሳታፊነት መጠን ፍ/ቤቱ እንደሚከተለው መርምሮታል::

1ኛ ተከሣሽ ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ድርጊትም ሲፈፅሙ የድርጊቱ ተካፋይ ስለመሆናቸው በማስረጃ የተረጋገጠ ቢሆንም በቀበሌዎች እና በከፍተኞች የተፈፀሙት የቀይሽብር ግድያዎች በሚፈፀሙበት 1ኛው ተከሣሽ ቀጥታ ተሳታፊ እንዳልነበር ከልዩ ዐ.ህግ የፅሁፍ ማስረጃዎች ልንረዳ ችለናል:: 1ኛው ተከሣሽ በወቅቱ ቀይሽብር እና ነጭ ሽብር እየተባሉ ስለሚጠሩት ሁኔታዎች በሚመለከት በጥቅሉ አንዳንድ ትዕዛዝ አዘል ደብዳቤዎች ለቀበሌዎችና ለከፍተኞች ያስተላልፋ ቢሆንም የእነዚህ ደብዳቤዎች ይዘት 1ኛ ተከሣሹ በወቅቱ በየቀበሌው እና ከፍተኞች ለተፈፀመው ቀይ ሽብር ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆናቸውን የሚያመለክቱ እንዳልሆኑ ከልዩ ዐ.ህግ የሰነድ ማስረጃዎች ልንረዳ ችለናል:: በመሆኑም 1ኛ ተከሣሽ፣

1/ ሰዎች በየቀበሌው በከፍተኞች እና በሸዋ ክ/ሀገር በተለያዩ አውራጃዎች እና ወረዳዎች በቀይሽብር ሲገደሉ በወቅቱ ጉልህ ሚና እና በቀጥታ ጉዳዩን ይፍፅሙ

ለትክክል ግልባጭ



46

የነበሩት የድርጊቱ አቀናባሪዎች እና ፈፃሚዎች ቀበሌዎች፣ ከፍተኞች እና ሌሎች ሕዝባዊ እና መንግስታዊ ድርጅቶች ሲሆን 1ኛ ተከሣሽ በወቅቱ በጉዳዩ ቀጥተኛ የሆነ ተሳትፎ ያልነበራቸው መሆኑ፣

2/ 1ኛ ተከሣሽ ጥፋተኛ በተባሉበት የወንጀል ድርጊቶች የተመለከቱት ተጐጂዎች በሚያዙበት እና ምርመራ በሚደረግላቸው ጊዜ ተሳትፎ ያልነበራቸው መሆኑ እና

3/ 1ኛ ተከሣሽ ጥፋተኛ በተባለት የወንጀል ድርጊቶች የተመለከቱት ተጐጂዎች ላይ የግድያ እርምጃ ሲወሰን በውሳኔዎቹ ቀጥተኛ ተሳትፎ ያልነበራቸው መሆኑ ከእነዚህ ሁኔታዎች በመነሳት 1ኛ ተከሣሽ ጥፋተኛ በተባለት የወንጀል ድርጊቶች ያላቸው አስተዋፅኦ ወይም በድርጊቶቹ ያላቸውን የተሳታፊነት ደረጃ ፍ/ቤቱ ሲመዝነው አነስተኛ የተሳታፊነት ደረጃ ያላቸው መሆኑን ፍ/ቤቱ ሊረዳ ችሏል።

በተጨማሪም 1ኛ ተከሣሽ ያቀረቡአቸው የሰውና የሰነድ የመከላከያ ማስረጃዎች 1ኛ ተከሣሽ በቀይ ሽብር ዘመን የብዙ ዜጐች መብት እንዳይጋፋ አስተዋፅኦ ያደረጉ መሆኑ፣ በተለያዩ ሁኔታዎች በሰዎች ላይ የሚደረገውን እንግልት እና የመብት ረገጣ በፅኑ ይቃወሙ የነበሩ መሆኑን፣ በህገ-ወጥ መንገድ የታሰሩትንና በቀይሽብር እንዲሙቱ የተዘጋጁቱን ሳይቀር በማስፈታትና በማዳን ሰዎች በህገ-ወጥ መንገድ መታሰርና መገደል እንደሌለባቸው አጥብቀው በመከራከር ብዙ አስተዋጽኦ ያደረጉ በስልጣን ዘመናቸውም ለህብረተሰቡ የመስጠት ማህበራዊ ግልጋሎቶች እና ሌሉች አቅርቦቶች እንዳይቋረጡ በመታገል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ቅን አሳቢ በህብረተሰቡ ዘንድ መልካም ስምና ዝና ያተረፉ መሆናቸውን አስረድተዋል። ፍ/ቤቱ ይህንንም ከግንዛቤ ውስጥ አስገብቷል። ከእነዚህ ሁኔታዎች በመነሳት ፍ/ቤቱ በ1ኛ ተከሣሽ የሚጣለው ቅጣት ቀሎ ሊወሰን እንደሚገባ አምኖበታል።

2ኛ ተከሣሽን በሚመለከት ከልዩ ዐ.ህግ የሰነድ ማስረጃዎች ለመረዳት እንደሚቻለው በወቅቱ ማለት በቀይ ሽብር ዘመን የቀበሌ የአብዮት ጥበቃዎች ፀረ-አብዬተኞችን ለመደምሰስ እንዲችሉ ትጥቅ እንዲሰጣቸው በማሳሰብ እና ሁኔታዎችን በማመቻቸት እንዲሁም በፀረ-አብዬተኞች የሚተኩሱት ጥይቶች በሚመለከት ሪፖርት እንዲደረግለት በማሳሰብ ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ድርጊት በሚፈፀምበት ወቅት የድርጊቱ ተካፋይ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም በየቀበሌው እና ከፍተኞች ሰዎች ለቀይ ሽብር አላማ ሲያዙም ሆነ ምርመራ ሲደረግባቸው የተሳታፊነት ሚና ያልነበረው መሆኑ፣ ሰዎች በቀይ ሽብር እንዲገደሉ ውሳኔ ሲተላለፍባቸው በውሳኔው ምንም ሚና ያልነበረው በመሆኑ የድርጊቱ ዋና አቀናባሪዎችና ፈፃሚዎች ሌሎች አካላት በመሆናቸው ከእነዚህ ሁኔታዎች በመነሳት 2ኛ ተከሣሽ ጥፋተኛ በተባለት የወንጀል ድርጊቶች ያላቸው አስተዋፅኦ ወይም በየድርጊቶቹ ያላቸው የተሳታፊነት ደረጃ ሲመዘን አነስተኛ የተሳታፊነት ደረጃ ያለው መሆኑን ፍ/ቤቱ ሊረዳ ችሏል።

ለልትክክል ግልባጭ



47

3ኛ ተከሣሽ በስራና ከተማ ልማት ሚ/ር የመለዩ ሰባሽ ተወካይ ሆኖ በሚሰራበት ወቅት ቀበሌዎች በተለያዩ ሰዎች የቀይሽብር እርምጃ በሚወስዱበት ዘመን ለቀበሌ የአብዮት ጥበቃ የትጥቅና እና የሌሎች ቁሳቁሶች እንዲያገኙ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የወንጀል ድርጊቶች ሲፈፀሙ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የድርጊቱ ተካፋይ የነበረ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም በየቀበሌዎች በየከፍተኛ ሰዎች ለቀይሽብር አላማ ሲያዙ እና ምርመራ ሲደረግባቸው ምንም ሚና ያልነበረው መሆኑ፣ ሰዎች በቀይሽብር እንዲገደሉ ውስኔ ሲሰጥ በውሳኔው ምንም ሚና ያልነበረው መሆኑ ከእነዚህ ሁኔታዎች 3ኛ ተከሣሽ ጥፋተኛ በተባሉበት የወንጀል ድርጊቶች ያላቸው አስተዋፅኦ ወይም በድርጊቶቹ ያላቸው የተሳታፊት ደረጃ ሲመዘን አነስተኛ የተሳታፊነት ደረጃ ያለው መሆኑን ፍ/ቤቱ ሊረዳ ችሏል::

በዚህም መሠረት ተከሣሾችን ያስተምራል ያስጠነቅቃል ሌሎች ተመሳሳይ የወንጀል ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ ያስጠነቅቃል ብሎ ፍ/ቤቱ በገመተው መሠረት በተከሣሾች ላይ የሚከተለውን የቅጣት ወሳኔ ሰጥቷል::

- 1ኛ ተከሣሽ ኰ/ል ደበላ ዲንሳ በ13/አስራ ሦስት/ አመት ፅኑ እስራት
- 2ኛ ተከሣሽ አቶ አበራ የማነአብ በ10/አስር/ አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ
- 3ኛ ተከሣሽ ኰ/ል ሮንዳሳ ቢራቱ በ13/አስራ ሦስት/ አመት ዓምት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ

በማለት በአንድ ድምፅ ወስነናል::

በተጨማሪም ሁሉም ተከሣሾች የእስራት ጊዜያቸውን ከጨረሱ በኋላ ለ3/ሦስት/ አመታት ከማናቸውም ማህበራዊ መብቶቻቸው እንዲታገዱ በማለት ወስነናል:: ሁሉም ተከሣሾች ከዚህ በፊት የታሰሩበት እንዲታሰብላቸው ብለናል:: ማረሚያ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲያስፈፅም ታዟል::

መዝገቡ የተወሰነ ስለሆነ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ::

10/12/97 10-12-97

ስለትክክለኛ ግልባጭ

**የዳኞች ፊርማ፣ ሙስጠፋ አህመድ**

**ሰለሞን አረዳ**

**ሐፊዝ አባጀማል**



48